# በአዲስ ዓመት አዲስ ልማታዊና ሰላማዊ ትልሞች

ቶሎሳ ኡርጌሳ

Utolosa@yahoo.com

የሰው ልጅ አሮጌውን ዓመት ሸኝቶ ወደ አዲስ ዓመት ሲሸጋገር አዲስ ህይወትን፣ ተስፋንና ራዕይን ይሰንቅ ዘንድ ተፈጥሮአዊ ባህሪው ግድ ይለዋል። ምናልባትም አዲሱ ዓመት ህይወትን እንደ አዲስ ለመጀመር የሚታሰብበት፣ ከአሮጌው ዓመት አላስፈላጊ ጉዳዮች ለመራቅ ቃል የሚገባበት፣ ከነጠላ ወደ ጣምራ ህይወት ለመሸጋገር የሚታለምበት አሊያም አዲስ ዓላማና ግብ ይዞ የዕቅድ "ቀነ-ቀጠሮ" የሚወጠንበት ሊሆን ይችላል።

"የሰይጣን ጆሮ አይስማውና በአዲሱ ዓመት ይህን ከውናለሁ፣ ይህን ፈፅማለሁ" የሚል ተስፋ በበርካታ ሰዎች ህሊና ውስጥ እስከ በዓሉ ዋዜማ የመጨረሻዋ ሰከንድ ድረስ መመላለሱ አይቀርም። ታዲያ ይህ ተስፋ፣ ተስፋ ብቻ ሆኖ መቅረት የለበትም። በተስፋው ውስጥ የግለሰቡ ቁርጠኝነት መታከል አለበት። ከቁመት በላይ ተሰቅሎ የተንጠለጠለውን ዳቦ ለማውረድ ሊገኝ የማይችልና የሌለን መሰላል ማሰብ አያስፈልግም። መሰላሉ እርግጥም ሊደረስበት የሚችልና ወደ መሰላሉ የመውጣት አቅምም መኖሩ በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት። ስለሆነም ተስፋው ምናባዊ ብቻ እንዳይሆን ግለሰቡ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ነገርን ብቻ ነው ማሰብ ያለበት።

እርግጥ ተስፋ የሌለው ሰው በነሲብ ካልሆነ በስተቀር በታቀደና በሚታወቅ ግብ ሊኖር አይችልም። አንዳንድ ግለሰቦች "ስለ ነገ አታስብ፣ ቀኑ ለራሱ ሲል ያስባል" የሚሉት የጨለመና ራዕይ አልባ አባባል፣ የህይወት ጭላንጭል ተስፋ እንኳን በውስጡ ያልያዘ ነው። ከዚህ ባሻገርም የግለሰቦችን የ"ነገ" ቀን "ህልም" የሌለው እንዲሆን የሚያደርግና "የነገ ሰውነትን" የሚያሳጣ ነው። ሰው በባህሪው ዛሬ ምሽት ወደ መኝታው ሲሄድ፣ ነገ የሚባል ቀንን ለማየት በውስጡ ተስፋን ሰንቆ ነው። ነገን በአዲስ ህይወት፣ በአዲስ የመኖር ጉጉት፣ በአዲስ ልማታዊ ትልም ና ሰላም፣ በአዲስ ቀንነት በመናፈቅ።…

…ነገን አለመኖር በሰው ልጅ ሰብዓዊ ባህሪ ውስጥ የሌለ የኑባሬው ዓለም ዕውነታ አንድ አንጓ ነው። ለነገ የማያስብ፣ ነገን በዛሬ ውስጥ የማያልም፣ የህይወትን ጣፋጭ ገፅታ አሹልቆ የማያይ እንዲሁም ነገን ሲያስብ ውስጡ በሐሴትና በፍሰሐ የማይሞላ ከቶ ማን ይኖር ይሆን?...አበው "የነገ ሰው ይበለን" የሚሉትስ ለዚህ አይደለምን?...እንዴታ!

…እርግጥ ነገን “ማለም” ዛሬን በተስፋ ውስጥ ሆነን እንድንኖር ያደርገናል። ይሁንና “ህልሙ” በገሃዱ ዓለም ውስጥ ያለን ዕውነታ የሚያመላክት፣ ከወዲሁ የሚታይና የሚዳሰስ እንጂ፤ በህልምነቱ የምናውቀውን የማታውን ዓይነት እውነተኛ ህልም መሆን የለበትም። በመሆኑም ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ስለ ነገ የምናስበው አዲስ “ህልም” ተጨባጭ መሆን አለበት። “እዮሃ አበባዬ፣ መስከረም ጠባዬ” ተብሎ አዲሱን ዓመት “የከርሞ ሰው ይበለን” ብለን ስንቀበል፤ በግለሰብ ደረጃ የምናቅደው አዲሱ “ህልማችን” የሚደረስበትና ሰላማዊ መሆን እንዳለበት መዘንጋት አይኖርብንም።

የማይደረስበትና ሰላማዊ ያልሆነ “ህልም” ቅዠቱ አያስተኛም። ውስጣዊ ቀውስንና ጥፋትን እንጂ ዕድገትንና ብልፅግናን አያመጣም። በመሆኑም በ2006 ዓ.ም የምናልመው “ህልም” ልኬቱና ስኬቱ ማግኘት የምንችለውን ብቻ ነው መሆን ያለበት። በፖለቲካው፣ በማህበራዊውም ይሁን በምጣኔ-ሀብቱ መስክ የሚታሰቡ ጉዳዮች የስኬት ልኬታቸው የነገ ሰው የመሆን ህልምን ማንፀባረቅ ይኖርባቸዋል። “ወደፊት የማይሄድ፣ ወደ ኋላ እየተራመደ ነው” እንዲል ደራሲ በዓሉ ግርማ፤ በ2005 ዓ.ም ከነበርንበት ቦታ ቢያንስ በተወሰኑ ሜትሮች ፈቀቅ ማለት ይኖርብናል። ‘ከዚህ እንዳትነሳ’ ተብሎ ዕግድ የተጣለበት ሰው ይመስል ትናንተ በነበርንበት ቦታ ላይ ዛሬ መገኘት የለብንም። እናም የነበረን አመለካከት በአዲሱ ዓመት በአዲስ ምልከታ መቀየር ይኖርበታል። ለምሳሌ በ2005 ዓ.ም በፖለቲካው ረገድ በተቃውሞው ጎራ የታዩ የነበሩት ‘የስሞተኝነት’ አካሄዶች በ2006 ዓ.ም የቅኝታቸው ስልተ-ምቶች መለወጥ ያለባቸው ይመስለኛል። መደገምም አይኖርባቸውም…

…በሸኘነው አሮጌ ዓመት በተቃውሞው ጎራ ከተቀነቀኑት ‘የስሞተኝነት’ አካሄዶች መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፦ “ፍርድ ቤት ብይን የሰጣቸው አባሎቻችን ወንጀለኞች አይደሉም”፣ “የኢትዮጵያ ለጋሽ ሀገራት አሜሪካ ኤምባሲ ጠርተውን ችግሮቻችንን ነግረናቸዋል”፣ “ፓርቲያችን በደልና ወከባ እየደረሰበት ነው”፣ “እገሌ በሚባል አዳራሽ ውስጥ ስብሰባ እንዳናደርግ ተከለከልን”፣ “ሰላማዊ ሰልፍ መስቀል አደባባይ እንዳናደርግ ታገድን” የሚሉት ይገኙባቸዋል።…እነዚህ አባባሎች የሃሳቡ ባለቤቶች የሆኑትን የፖለቲካ ድርጅቶችን የሚመለከቱ ቢሆኑም፤ መሰረት በሌላቸው ማማረሮች ላይ የተመሰረቱ ‘ስሞተኝነት’ ናቸው። እርግጥ የአባባሎቹ ባለቤቶች ሰዎች በመሆናቸው አረረም መረረም የራሳቸው “ህልም“ ሊኖራቸው ይችላል። ግና ህልማቸው ተጨባጭና ሰላማዊ መሆን ያለበት ይመስለኛል። የፖለቲከኞቹ የነገ “ህልም” የማይጨበጥ (Abstract) ከሆነ

ውጤቱ ከፓርቲ ባለፈ ግለሰባዊ ኪሳራም ሊኖረው ይችላል። እርግጥ አምና የነበሩትን የስሞተኝነትና የማማረር ህልምን ዘንድሮ ለማሳካት መጣር ውድቀትን እንጂ ሐሴትን እንደማያመጣ ፖለቲከኞቹ ልቅም አድርገው የሚያውቁት ይመስለኛል። ምክንያቱም ይህን ዕውነታ የአስተሳሰቡ ባለቤቶች ባለፉት አራት ሀገራዊ ምርጫዎች በግልፅ የተረዱት መሆናቸውን መናገር ስለማይጠበቅብኝ ነው። ‘ለቀባሪው ማርዳት’ ኢትዮጵያዊ ባህል አይደለምና።...ውይ የእኔ ነገር ተሳሳትኩ እንዴ?...ይቅርታ! ውድ አንባቢዬ እባክዎን ‘ለተቀባሪው ማርዳት’ ብለው ቢያርሙኝ ወሮታ ከፋይ ነኝ።...

ያም ሆነ ይህ እየተጫጫነኝም ቢሆን በ2006 ዓ.ም የእነዚህ ሃሳቦች ባለቤቶች “ያደቆነ ሰይጣን...” የሚለውን ብሂል ያፈርሱታል የሚል እምነት አለኝ። ግለሰቦቹ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአዲሱ ዓመት ደግ ደጉን ያስባሉ ብዬም እገምታለሁ። ይህን ስል ግን በመሆኑም ያለፈውን ዓመት የ‘ስሞተኝነታቸውን’ ስልተ-ምት በሚከተለው መልኩ ቢቀይሩት ስል የአዲስ ዓመት ግላዊ ምኞቴን ለማስተላለፍ ይዳዳኛል። ታዲያ ስልተ-ምቱን ቅያሪ በፍርድ ቤት ጀምሬ በአደባባይ እንዲህ ባሳርገውስ?...“ፍርድ ቤት ብይን ከሰጣቸው አባሎቻችን ጥፋት ተምረናል”፣ “የኢትዮጵያ ለጋሽ ሀገራት የሀገራችንን ልማት በማገዝ ረገድ ወሳኝ ባይሆንም የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ ብለን እናምናለን። በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ግን ሊገቡ እንደማይችሉ እንገነዘባለን። ችግሮች ሲገጥሙንም የስልጣኑ ሉዓላዊ ባለቤት ለሆነው ህዝባችን ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እናስረዳለን፣ የውጭ ጣልቃ ገብነትንም አንጋብዝም”፣ “ካለተጨበጠ አሉባልታና የመንግስትን ስም ከማጠልሸት እንታቀባለን”፣ “በየትኛውም ቦታ ስብሰባ ስናደርግ ህጋዊ መስፈርቶችን እንከተላለን”፣ “ሰላማዊ ሰልፍ መስቀል አደባባይም ይሁን በሌላ ቦታ ስንከውን የህግ የበላይነትን እናከብራለን”...ሌላ...ሌላም።

አዎ! እንዲህ ዓይነቱ ሐቁን ያልሳተ፣ ተጨባጭ፣ ሰላማዊና የመግባባት ፖለቲከኝነት ለተሰለፉለት ዓላማና ግብ የሚያበቃ ነው። ይህም ለፖለቲከኞቹ፣ ለፓርቲያቸውና ለመላው ህዝብ የሚበጅ መሆኑ የሚታበይ አይደለም። ስለሆነም በአዲሱ ዓመት የተቃውሞው ጎራ ፖለቲከኞች የቅኝታቸውን ስልተ-ምት በዚህ ሁኔታ ቢቀይሩት (ምንም እንኳን ከአፈጣጠራቸውና ከባህሪያቸው በመነጨ “ህልማቸውን” ለማሳካት የሚችሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ባይኖራቸውም) ምናልባት ለነገ ተስፋ ሊኖራቸው ይችላል–የህዝቡን ቀልብ መሳብ ከቻሉ። እናም 2006 ዓ.ም የተቃውሞው ጎራ ፖለቲካ ከስሞተኝነት፣ ከማማረር፣ ከጭፍን

ጥላቻ፣ ከአሉባልታ፣ ከሁከት ናፋቂነት፣ ከበሬ ወለደ ድርሰት፣ ለህግ የበላይነት ተገዥ ካለመሆን…ወዘተ. የነፃ እንዲሆን አዲስ ሀገር በቀልና ልማታዊ "ህልም" መያዝ ያለበት ይመስለኛል–ከአድሮ ቃሪያ ፖለቲካዊ ዳንኪራ ለመዳን ከፈለገ።

የማህበራዊው መስክም ቢሆን ከዚህ የተለየ አይደለም። አንድ ሰው አዲሱን ዓመት ሲቀበል ራሱን ሰላማዊ ባልሆነ፣ በማይጨበጥና ከገሃዱ ዓለም ዕውነታ ጋር የማይገናኝ ጉዳይን "ካለመ" ከጉዳቱ ባሻገር የከፋ መዘዝንም ሊቀበል ይችላል። ታዲያ እዚህ ላይ አንድ ወዳጄ ያወጋኝን እውነተኛ ታሪክ ማንሳት ይህን አባባሌን ይበልጥ የሚያሰረዳልኝ ይመስለኛል። ነገሩ እንዲህ ነው።…የታሪኩ ባለቤት የሆነው የወዳጄ ባልንጀራ ተጨማሪ ገቢ የሌለው የመንግስት ሰራተኛ ነው። በወር ደመወዝ ብቻ የሚተዳደር። ይህ ሰው በአሮጌው ዓመት መገባደጃ ላይ በሚቀጥለው ዓመት ሃብታም መሆን አለብኝ ብሎ ይወስናል። እንግዲህ ይታያችሁ!…በወር ደመወዝ ብቻ የሚተዳደር ሰው ሌላ የመበልፀጊያ ዘዴ ከሌለው በስተቀር በምን ዓይነት ሁኔታ ሃብታም ሊሆን ይችላል ትላላችሁ?…ያም ሆነ ይህ ግን ግለሰቡ ሃብታም የመሆን "ህልሙን" አጠናክሮ በመያዝ ወጉን ለነገረኝ ወዳጄ፤ "አዲሱ ዓመት ሲመጣ ታየኛለህ፣ የእኔና የአንተ የአፍሪካና የአሜሪካ ልዩነት ያህል ነው የሚሰፋው!" በማለት የአዲሱን ዓመት መግባት በናፍቆት መጠባበቅ ይጀምራል።…

…አዲሱ ዓመትም ገባ።…መስከረምም ጠባ።…የዓመቱ መባቻ ተከታታይ ቀናት ውስጥ የወዳጄ ጓደኛ ከመስሪያ ቤቱ ተሰወረ።…ቢሮው ብቅ አላለም።…ግና ከእነ አካቴው አልቀረም። በወሩ አጋማሽ ላይ ግለሰቡ ለወዳጄ ስልክ ይደውላል። የስልኩ መልዕክትም "እስከ መስከረም 20 ቀን ድረስ ሃብታም ሆናለሁ" የሚል ነበር። ነገሩ ግራ ያጋባው ወዳጄ ስልኩ የተደወለበትን ቀን ለማወቅ እጆቹን ወደ ካላንደሩ ላካቸው–መስከረም 15 ቀን ይላል። በአምስት ቀን ውስጥ ጓደኛው እንዴት ሃብታም ሊሆን እንደሚችል ማሰላሰል ጀመረ–ምንም ነገር ግን ሊገለፅለት አልቻለም። እናም መስከረም 20ን እርሱም በተራው ይናፍቅ ጀመር።…ዳሩ ምን ያደርጋል?!–ጓደኛው መስከረም 20ን እንደናፈቃት ቀርቷል። …እንዴት?…ነገሩ ወዲህ ነው።…

…ይህ ሰው የሚያውቀው አንድ ግለሰብ እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ ያለ ጥንቃቄ ገንዘብ አውጥቶ ወደ ቤቱ በመሄድ ላይ ሳለ በወዳጄ ጓደኛና በግብረ-አበሮቹ ተዘረፈ። ግና ፖሊስ ባደረገው ጥብቅ ክትትል ዘራፊዎቹ ተይዘው ዘብጥያ ወረዱ። የወዳጄ ጓደኛም የሃብታምነት "ህልሙን" ደግሞ ደጋግሞ ማረሚያ ቤት ውስጥ እንዲያየው ተገደደ።…"ይህ ሰው

ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት በመሆኑ፣ የቤተሰቦቼን የአዲስ ዓመት ተስፋ ይዞ ነው እስር ቤት የገባው" ሲል በምሬትና በፀፀት ወዳጄ አውግቶኛል።...ለመሆኑ እንዲህ ዓይነቱን "ህልም" ከቶ ምን እንለው ይሆን?...

አዎ! ማንም ሰው ነገ አገኘዋለሁ ብሎ የሚያልመው ስኬት በራሱ ወዝና ላብ ጥሮ ግሮ የሚያገኘው የድካሙ ዋጋ ነው መሆን ያለበት። ሌላው የለፋበትን ሃብት በመቀማት ወይም የራስ ያልሆነን ሃብት በአንድ ቀብ በአቋራጭ በማግኘት መመኘት አደጋው ህይወትን እስከ ማጣት ድረስ ሊያደርስ ይችላል። አዲስ ዓመት ሲመጣ "ማለም" ያለብን ነገር በአሮጌው ዓመት የነበሩብንን ችግሮች የሚያቃልል፣ ጠንካራ ጎኖችን ይበልጥ ለማጠናከር የሚያስችል እንዲሁም በሰላማዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት። ይህን ለማከናወንም "ህልማችን" ልኬት ያለውና በራስ አቅም ሊፈፀም መቻልና አለመቻሉን መልሰን መላልሰን መፈተሽ ይኖርብናል። ታዲያ "ህልማችን" የልኬታውን ፈር ስቶ እንደ ወዳጄ ባልንጀራ ከመሬት ተነስቶ በአንዴ ሃብታም ለመሆን የመሻት ዓይነት ከሆነ፤ ነባራዊ ዕውነታው አንድን ልጃገረድ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የመጥቀስ ያህል የማይታለም ነው የሚሆነው። በመሆኑም በአዲሱ ዓመት ያልተገባ ጥቅምን (ሙስናን) በማውገዝና ሰላማዊ ሆነን የሰውን ጥሪት ባለመመኘት አዲስ ተስፋን መሰነቅ አለብን። በተለይም ሙስና "በነገ ሰውነታችን" ላይ ጉልህ የጥፋት አሻራ የሚያሳርፍ እንዲሁም የህዳሴ ጉዟችንን የሚያዘገይ በመሆኑ 'እዛው በፀበልህ' ብለን በቁርጠኝነት ልንታገለው ይገባል።

ታዲያ እዚህ ላይ ስለ ሙስና ሳነሳ አንድ አባት መፅሐፍ ቅዱስን ዋቢ አድርገው ያጫወቱኝን ወግ አስታወስኩ። እኚህ አባት "ሙስናን እንኳንስ እኛ ኢየሱስ ክርስቶስም ይቅርታ አላደረገለትም" በማለት ነበር ወጋቸውን የጀመሩልኝ። እርግጥ በተቆላመጠ ስሙ ዛሬ 'ሙስና' እየተባለ የሚጠራው የያኔው 'እጅ መንሻ' ወይም 'ጉቦ' የብዙ ዓመታት ታሪክ ያለው መሆኑን አጫውተውኛል። በየትኛውም የዓለም ክፍል እንደ ቫይረስ እየተስፋፋ፣ ድሃውን እያቀረቀዘ፣ ጥገኛ ሃብታሙን የሚያበለፅግ መሳሪያ መሆኑንም ጭምር።

...ሁኔታው 'እጅ መንሻ' ወይም 'መማለጃ' እየተባለ በመፅሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥም ከአይሁዳውያን ሊቃውንት ጀምሮ እስከ እየሱስ ክርስቶስ ሃዋሪያት ድረስ ለነበሩ መንፈሳውያንም ፈተና እንደነበር በአባታዊ አንደበታቸው ነግረውኛል። እንደ እርሳቸው አባባል፤ በዚያን ወቅት መንፈሳውያኑ ገንዘብ ያታልላቸው ነበር፤ መለማመጃም ከምዕመኖቻቸው ይቀበሉ ነበር። የአስቆሮቱ ይሁዳ 30 ዲናሩንም ይሁን አሳልፎ የሰጠውን

የኢየሱስ ክርስቶስን የመጨረሻ ሳያይ ራሱን ግራር ላይ ሰቅሎ ተገኝቷል። የሐጢያቱ መጨረሻም አላማረምና ክርስቶስ በትንሳኤው ሌሎች ሃዋሪያትን ሲያነፃ፣ ይህን ዕድል ለአስቆሮቱ ይሁዳ አልሰጠውም—ታዲያ ይህ ታሪክ የሚያስተምረን ነገር ቢኖር፤ የዛሬው ‘ሙስና’ ከምድራዊ ተጠያቂነት ባለፈ ሰማያዊ ቁጣን የሚያስከትል መሆኑን ያስረዳናል ሲሉ አውግተውኛል።…

…እናስ በአዲሱ ዓመት በተስፋነት የምንይዘው አዲስ “ህልም” ይህን ምድራዊም ይሁን ሰማያዊ ውግዘት ያለበትንና አደጋው በግለሰብ፣ በቤተሰብ ብሎም በሀገር ደረጃ የከፋ መዘዝ የሚያስከትለውን አስተሳሰብና ድርጊት መጠየፍ እንዲሁም የተግባሩ ተባባሪ ባለመሆን የሚያስችለን ሰናይ ዓመት አድርገን ብናልመውስ?—አዎ! የዚህ ፅሑፍ አንባቢ በ2006 ዓ.ም አዲስ ዕቅድ ሲይዝ የተጀመረውን ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት እጅና እግሩን ጠፍሮ አላራምድ ሊለው የሚችለውን ይህን የነቀዘ ተግባር በፅናት ለመታገል ለራሱ ቃል የሚገባበት ጊዜ መሆን አለበት ባይ ነኝ። በዕቅዱ ውስጥም ይህን የዕድገት ፀር ተግባርን ባለማካተትም ጭምር። ይህን ስንከውንም “ህልማችን” በራስ ጥረት የሚገኝና ሀገራዊ ዕድገታችንን ቀጣይነት ይበልጥ የሚያረጋግጥ ልማታዊና ሰላማዊ ይሆናል።

የተለያዩ ሰዎች በአዲሱ ዓመት ‘በአዲሱ ዓመት ከደባል ሱስ እላቀቃለሁ፣ የትዳር አጋር እፈልጋለሁ፣ በስራዬ አዲስ የደረጃ ዕድገት ለማግኘት እጥራለሁ…ወዘተ.’ የሚሉ ዕቅዶች ሊኖሯቸው ይችላል። ዕቅዳቸውን ለማሳካትም ባቀዱት መጠን መንቀሳቀሳቸው አይቀርም። ስፋትና ጥልቀቱ እንዲሁም ይዘቱ ይለያይ እንደሆነ እንጂ፣ መንግስትም ቢሆን ከዚህ የተለየ አያደርግም። አዲሱ ዓመት መንግስት ያቀደው የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተጠናክሮ የሚቀጥልበት ነው።

እንደሚታወቀው ባለፉት ሁለት ተኩል ዓመታት ዕቅዱ በተሳካ ሁኔታ ተተግብሯል። የዕቅዱ ዋነኛ ተዋናይ የሆነው የሀገራችን ህዝብ ለዚህ ስኬት የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል። ህዝቡ በእነዚህ የልማት ዕቅዱ ዓመታት የስራ ባህሉንና ተነሳሽነቱን እንዲሁም የቁጠባ ባህሉን አዳብሯል። በዚህም የተገኙትን የቅርብ ጊዜ ውጤቶች በምሳሌነት በጥቂቱ መመልከት እንችላለን። በቅርቡ ‘ስትራትፎር’ የተባለ ተቋም፤ ባካሄደው ጥናት የቻይና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እየተቀዛቀዘ መምጣቱን ተከትሎ በቀጣይ ኢትዮጵያን ጨምሮ 16 የአለም አገራት ይህንኑ ዘርፍ በበላይነት ይመራሉ ሲል ባካሄደው ጥናት እማኝነቱን ሰጥቷል።

ተቋሙ ያካሄደው ጥናት እንደሚጠቁመው በሚቀጥሉት ጊዜያት ኢትዮጵያን ጨምሮ 16 የዓለም ሀገራት በቻይና የበላይነት ተይዞ የነበረውን የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የበላይነት የሚቆጣጠሩት ባላቸው ርካሽ የሰው ጉልበትና በርካታ አምራች ወጣት ኃይል ስላላቸው መሆኑን ከመግለፅ ባሻገር፤ በሀገራቱ የሚታየው ፖለቲካዊ መረጋጋትም ለዘርፉ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱንም አስረድቷል፡፡ ከፍተኛ ውጤት የተመዘገቡባቸው ዘርፎች የጫማ ምርት፣ የሞባይል እና የጨርቃጨርቅ ውጤቶች ከፍተኛ ደረጃ ተስፋ ያላቸው መሆናቸውንም አመልክቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አጎዋ በተሰኘውና አሜሪካ ኢትዮጵያን ጨምሮ ለተለያዩ የአፍሪካ አገራት በሰጠችው ከቀረጥ ነጻ የገበያ ዕድል አማካኝነት ሀገራችን ወደ አሜሪካ የላከቻቸው የአበባ፣ የቆዳና ሌጦ፣ ተሰፍተው ያለቁ ጫማዎች እንዲሁም ኑግን ጨምሮ የተለያዩ የቅባት እህሎች መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ እያደገ መምጣቱ በቅርቡ ሀገራችን ውስጥ በተካሄደው የአጎዋ ስብሰባ ላይ ተገልጿል፡፡

በስብሰባው ላይ ኢትዮጵያ የአጎዋን እድል በመጠቀም በአገሪቱ ለሚገኙ አምራች ድርጅቶች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ መሆኗም ተመልክቷል። እንዲሁም "የኢትዮጵያ መንግስት የተሰፉ ልብሶችን የሚያመርቱ ድርጅቶችን አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ስራዎችን ይሰራል፤ አበቦችን ወደ ውጭ ለሚልኩ ድርጅቶችም መሬት እና ብድር ያመቻቻል፤ በዚህም የተነሳ ባለሀብቶችን በመሳብ የወጪ ገበያውን በእጅጉ አሳድጓል፤" ሲሉ የጉባኤው ተሳታፊዎች እማኝነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎንም ሀገራችን ታላቋ የኑግ አቅራቢ መሆኗም ተገልጿል ፡፡

እርግጥ ሌሎቹን ስኬቶች ትተን እነዚህን ሁለት ጉዳዮች ብቻ ስናይ፤ በልማታዊው መንግስት ዕቅዶች የሚመራው የሀገራችን ህዝብ ሁለንተናዊ የስራ ባህሉን አዳብሮ ውጤታማ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም። ታዲያ በአዲሱ ዓመትም ይህን የዳበረ ሁለንተናዊ ባህል ይበልጥ ማጎልበት ያስፈልጋል። መንግስት የቀየሰው ዕቅድ ሁላችንንም በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርገን በመሆኑ፤ ለስኬታማነቱ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን በግል ዕቅዳችን ውስጥ ጭምር ማካተት ይኖርብናል።

በተለይም የስራ ባህልንና ተነሳሽነትን ማዳበርና ማጎልበት ለ2007 ዓ.ም የምናስተላልፈው ጉዳይ መሆን የለበትም። ለነገሩ ታታሪውና ሰራተኛው ህዝባችን በዚህ አይታማም። ይሁንና የበለጠ ለማደግና የድህነት ካባችንን አውልቀን ለመጣል የስራ

ተነሳሽነታችንንና ባህላችንን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ይኖርብናል። በፅልመት አረንቋ ውስጥ የሚደናበሩ አደናቃፊዎችንና የውጭ ሃይሎች ተላላኪዎችን ብሎም ምንደኞችን ሳይሆን፣ የመንግስትን ተከታታይ ልማታዊና ሰላማዊ ጥሪዎችን በማዳመጥና ፈጣን ምላሽ በመስጠት "የነገ ሰውነታችንን" ማብሰር አለብን።

እርግጥ በሀገር ደረጃ ያለው ተጨባጭና ሊደረስበት የሚችል "ህልም"፤ ግለሰባዊ "ህልማችን" ዕውን እንዲሆን የሚያደርግ ነው። ስለሆነም መንግስት በፈጠረው ምቹ ሁኔታ በተደራጀ አኳኋን ማናቸውንም ስራዎች ይበልጥ ሳንንቅ ብንሰራ፣ ይበልጥ ስራ ጠባቂዎች ሳይሆን ፈጣሪዎች ብንሆን፣ የዛሬን ስራ ይበልጥ ዛሬ ብቻ ብናከናውን፣ የቁጠባ ህላችንን ይበልጥ ብናጎለብት…ወዘተ.፤ "ነገአችን" ከተስፋነት ባሻገር ዕውን ሊሆን እንደሚችል በእርግጠኝነት ብናገር የምሳሳት አይመስለኝም—"ጅማሬው መጨረሻውን ያሳያል" እንዲሉት ነውና።

የትናንት ታሪክ በታሪክነቱ ጠቃሚ ቢሆንም፣ እርሱን እያወሳን ብቻ ልንኖር አንችልም። በዛሬ "ህልም" ግን ነገን ብሩህና ጣፋጭ ማድረግ እንችላለን። እናም 'ትናንት እንዲህ ነበርን' ከማለት ይልቅ፤ 'ዛሬ እንዲህ ነን፣ ነገ ደግሞ እዚያ እንደርሳለን' የሚል ተስፋን መያዝና ለተግባራዊነቱም መረባረብ ከአዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ መከናወን ያለበት ተግባር መሆኑን በአዕምሮአችን ባህር መዝገብ ውስጥ መፃፍ ይኖርብናል። እኔም እንደ ዜጋ በአዲሱ ዓመት ሁላችንም በግለሰባዊ ዕቅዳችን ውስጥ ከላይ የጠቀስኳቸውን ተግባሮች በበጎ ጎናቸው እንደምናካትት ያለኝን ተስፋ በመግለፅ፤ የነገ ሰው የሚያደርገንን አዲሱን "ህልማችንን" ዛሬ መጀመር ይኖርብናል እላለሁ። በአዲሱ ዓመት አዲስ ልማታዊና ሰላማዊ ትልሞችን ሰንቀን። መልካም በዓል።